723. ቀምን በቆጥ – ከመሸ አትሸሽ ውሪን ሲቆጥ

. ከመሸ አትሸሽ፣ ሲያልቅ አትቆጥብ

.. አባት እያለ አጊጥ ጀንበር እያለች ሩጥ

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

724. ቀምን ዎጦጥ ዎንቲን ዝንአጥ

. ከመሸ አትሩጥ ከነጋ አትተኛ

.. ጊዜ ወርቅ ነው ግን ሃላፊ ነው

725. ቀረ ምሽርዮ ጎደሬ ሚስ

. አዋቂ ነች የተባለችዋን ጅብ ይበላታል

.. ከፎከረ የጠረጠረ

726. ቀረ ምሸሬ ዘሬ መጨ ነአ ዬሌስ

. የጐበዝ ሴት ዘር ሴት ልጅ ይወልዳል

.. ከነብር ዘር ድመት ይወለዳል

.. ከነብር ሆድ አነር ይወለዳል

727. ቀረ ሻሻ ጮንቻ ላፈ ኦይሰይ ጌልዶ ቱክየን ፓጨ

. ደህና አድርጐ ቆሎ የሚቆረጥመውን ትንሽ ቅቤ በገባበት ቡና ገምት

.. የሽሮ ድንፋታ እንጀራ እስቲቀርብ ነው

728. ቀረ ቀረ ግን ቀርያ ሊጥያ ዳጠውሱ

. ጐበዝ ጐበዝ ቢሏት ሴትየዋ እርሾ ትድጣለች

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቁስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ...

729. ቀረ ቀረ ግን ዬሆ ከሬን ጥቶ ሱቀውሱ

. ጐበዝ ያሏት ለቅሶ ቤት ደጅ ተቀምጣ ጥጥ ትፈትላለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቁስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

730. ቀር ዎረ ግዴነ

. ጉበዝና መግደል አይደለም

.. መግደልና መፎከር ለየቅል ናቸው

731. ቀርያ መራ ዎረውሱ

. ባለሙያ ነች ያሏት ሴት ጥጃ ሳታጠባ ትገላለች

. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

732. ቀርያ ቀምስየን ሽየደ ነጠላን ቁጨውሱ

. ባለሙያ ቀሚሷ ላይ አርታ በነጠላዋ ትጠርጋለች

.. የባለጌ ምራቅ ከፍ ሲል እደረቱ ዝቅ ሲል እጉልበቱ

.. የቄስ ሚስት...

733. ቀርያ ተ ኣዬ ሸርቄ ጥንቄስ ገውሱ

. ባለሙያ ሴት የናቴ ጉያ ይገማል ትላለች

.. እውቀት ሲበዛ ያሳብዳል

734. ቀረይ ቀጢ፣ ቀጨይ ቀጢ፣ ግየ ሃትያ ቀማ ጎገይሱ

. ቀረሮ ወይም ሐረግ አይጠልፈኝም (አያደናቅፈኝም) የምትል ውሃ ማታ ማታ ትፈሳለች

.. አንበሳ ምን ይበላል ተበድሮ ምን ይከፍላል ማን ተናግሮ

735. ቀራ ቀረይ ዎሬስ

. ኃይለኛውን ኃይለኛ ይገለዋል

.. ለጐበዝም ጐበዝ አለው

736. ቀራ ደርየ ኩተን ሽየውሱ

. አዋቂ ነኝ ባይ ኩታዋ (ነጠላዋ) ላይ ታራለች

.. ጐበዝ የተባለ በሬ ቀንበር አንጥፎ ይተኛል

737. ቀራ ደርያ ቁይጦ፣ አብራሜ ሀርያ ሴጦ

. እውቀት የምታበዛ ከሲታ ነች፣ የአብርሃም አህያ ቀዥቃዣ ነች

.. እጅግ ስለት ይቀዳል አፎት፤ እጅግ ብልሃት ያደርሳል ከሞት

738. ቀራ ጎንደሌ ቃቀን ዎሬስ

. የጀግና ጋሻ በአምሮት ይገላል

.. ምኞት ያከሳል

739. ቀሬ ዶና ኤጬሬ ቀንጤስ

. የአዋቂ ነኝ ባይዋን አፍ አይጥ ይቆርጣል

.. አፍ ያለው ጤፍ ይቆላል

740. ቀሬስ ቀሜስ፣ ኤዩስ ዎንቴስ

. ለጐበዝ ይመሽባታል ለሰነፍ ይነጋላታል

.. ለሞኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ

741. ቀናትየው ኩንዶጌ ሀይቆጋ መለቴስ

. ለምቀኛ ከወደቁ የሞቱ ይመስለዋል

.. ጠላት በጥርስ ሲገኝ

.. ጠላት ይቀባል ጥላት

742. ቀንተ ቀጠነይ ገልባ ቦላፔ አሹዋ ቆሬስ

. የማይረባ ሰው ከቆዳ ላይ ልፋጭ ይለቅማል

.. የማይበላ የለም የማይጠግብ ባሰ

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

743. ቀንተ ጌለእያ ገካ ገካረ ዎሄ ኮከውሱ

. አጭር ልጃገረድ ከደረሰው ጎረምሳ ሁሉ ጋር አደንጓሬ ትቀቅላለች

.. አጭር ሰው አንቱ ሳይባል ይሞታል

744. ቀንገነ ኤቅድ ኔ ቦሎዋ ጦሰው መገነ ጌስ

. ሊረግም አስቦ በአማትህ አምላክ ይላል

.. አያጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

745. ቀንጥን ሜሌስ ውርስን ውሬስ

. ለቆረጠ ይደርቅለታል ለጨረሰ ያልቅለታል

.. ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል

746. ቀንጠይኔ ጉተ፣ ጉጩኔ ጐተ

. መቁረጡም ሆነ ዋግም፡ቱ ቀላል ነው

.. ነገሩ ነው እንጂ ጩቤ ሰው አይገዳም

.. ትገብት ነው ትርፉ

747. ቀይያ ሚዳጌ ቀኪዲ ዎሬስ

. ጥሬ የበላ ረግጦ ይገላል

.. የበላ በለጠኝ የሮጠ አመለጠኝ

748. ቀዬ ማጋ አ አቀንተይ ፓጭን፣ ጃኑዋ ማየባ አ ሀሼ ፓጩስ

. ጥሬ የበላውን ሆዱ ይታዘበዋል ጃኖ የለበሰውን ጅርባው ይታዘበዋል

.. አይን አይቶ ልብ ይፈርዳል

749. ቀጠ ከነይ ነገረንቻ ከሬን ሀይቂስ

. ክፉ ውሻ ከባላጋራ ደጅ ይሞታል

.. እንኳን ዘንቦብሽ ወትሮም ጤዛ ነሽ

750. ቀጠሬቴናሮ ኤክን የረይ በዩስ

. ያልተገረዘችውን ቢያገቡ ዘር ይበላሻል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

751. ቀጠነ አገነይ አቱዋ ቁንጡራስ

. ችጋራም ባል እንስራ ይቆነጥራል

.. ምን ያምጣ ድሃ ምን ያገሳ ውሃ

.. ስስታም ሰው አንድ ያንቀው አንድ ይወድቀው

752. ቀጤትየ ጌዴ አጉንታ ዬደ፡ስ

. የሚወላገድ እግር እሾህ ይረግጣል (ላይ ይወጣል)

. አለማረፍ ጣር ያበዛል

753. ቃላ መልአይ ቀሹዋን ዲእድ አትሰስ

. አንደበተ ርቱእ የሆነ ሰው እስር ቤት ሆኖ ያሰራል

.. መልካም ምላስ ቁጣን ታበርዳለች

754. ቃልቸይ ቀመ ቀንጌስ፣ ሰአይ ሀመ·ስ አርበ ዎንቴስ

. ውቃቢ ማታ ይራገማል፣ ሀሙስ ለአርብ ይነጋል

.. ሰኔና ሰኞ...

755. ቃርያ ማለዶ ቱሙዋ ቶከደ አመርስ ሶ በይደ ሾደደ ቢታበይ ነውአሾ ገውሱ

. ጦጣ ጥዋት ነጭ ሽንኩርት ተክላ ማታ ወደ ቤት ስትመለስ ነቅላ አይ የመሬት ነባር ይገርማል ትላለች

.. ሲ.ወልዱ አይታ በጠጢን ጣለች

.. ሲ.ያረጉ አይታ ዶሮ ታንታ ሞተች

756. ቃርያ ቀጠራ ጌለን ጨቸይ የገኑዋ ኤፈስ

. ጦጣ ሲ.ገረገ ቅማል አክፋይ ይዞ ይሄዳል

.. ያይጥ ምስክር ድንቢጥ

.. ግም ለግም አብረሀ አገግም

757. ቃርያ በርዮ ቀጠራ ጌለ ቢኡኩሽን አሰ አይፊያ አይቀውሱ

. ጦጢት ለራሷ ሳትገረገ የሌላውን አይን ትይዛለች

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

758. ቃርያ አሰ ቁልየው ማጡዋን አይፊያ ጨደረ ቶይሰይሱ

. ጦጢት የሰውን አይታ ቅንጭብ ተቀብታ አይኗን ታጠፋለች

.. ሲ.ሉ ሰምታ ዶሮ ታንቃ ሞተች

.. ሲ.ወልዱ አይታ በጠጢን ጣለች

759. ቃርያ አሰ ቁልየው አይፍያ አክርሳ ማታ ትየውሱ

. ጦጣ የሰውን አይታ አይኗን የቁልቋል ወተት ትቀባለች

.. ሲ.ወልዱ አይታ በጠጢን ጣለች

.. አይጥ የእመቤቷን ፀጉር አይታ ጆሮዋን ትቋጥራለች

760. ቃርያ አትዮ ዎዴ ባወሽን ቁማ ዎዴ ገከውሱ

. ጦጢት በእርሻ ጊዜ የለችም ግን ምግብ ሲቀርብ ከተፍ ትላለች

.. ቱሪናፋ ቱሪናፋ በስራ ጊዜ የለህ ከገበታ አትጠፋ

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

761. ቃርያ ጎበደ ጋሙዋ ቆርያ አይቀውሱ

. ጦጣ ስታይል የአንበሳን ጉረሮ ትይዛለች

.. አይጥ ሞቷን ስትሻ ስታበዛ ሩጫ፣ ሄዳ ታሸታለች የድመት አፍንጫ

762. ቃርያ ጭም አኒ ግን ታን ጭመ ገውሱ፣ ሾጋ ኤከነይ አኔ ግን ጉት ተነ ተ ኤከነ ገውሱ፣

. ጦጣ ሽማግሌ ማነው ሲባል እኔ ነኝ ሽማግሌ ትላለች፣ የጐደሬ ትራፊ ማን ይውሰድ ሲባል እኔ ትንሽ ነኝ እኔ ልውሰድ ትላለች

.. ኑሮ በዘዴ

.. አይጥ ነሽ እዩት ክንፌን ወፍ ነሽ እዩት ጥርሴን

763. ቃሬ ማተይ ሶ ጌሌነ ጋሼ አይተይ ከሬ ክዬነ

. የጦጣ ወተት እቤት አይገባም የጤፍ ቂጣ ውጪ አይወጣም

.. አያድርስ የባል ቢስ አያቅፍ አያንተርስ

.. ዱባና ቅል አበቃቀላቸው ለየቅል

764. ቃሬ ቁር ዶአ፣ ናኡ ብር ጉተ አጮ

. ጦጣ ትንሽ አውሬ ነው ሁለት ብር ትንሽ እዳ ነው

.. ፉት ቢሉት ጭልጥ

.. ለድሃ አታበድር ካበደርክም አታስቸግር

765. ቃሬ በቀ ኡንጨይ ሶ ጌሌነ ደዳ በቀ ማተይ ከሬ ክዬነ

. የጦጣ የአቴቴ ቆጮ እቤት አይገባም፣ የነጐድጓድ የስለት ወተት ውጪ አይወጣም

.. ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል

.. ሆድና ጀርባ

766. ቃቀይ ላፈቴስ

. መጓጓት (ምኞት) ያሳንሳል፣ ያከሳል

.. ምኞት ያከሳል

767. ቃቃ ደርየ ከነይ ኬተ ግዶን ሃይቁስ

. ምኞት የሚያበዛ ውሻ፣ እቤት ውስጥ ይሞታል

.. ምኞት ያከሳል

768. ቃቃ ደርየ ከንያ መቀ ግዶን ህይቀውሱ

. ተመኝ ውሻ አገዳ ውስጥ ትሞታለች

.. የማያዘልቅ ጸሎት ለቅስፈት

769. ቃቃትደ ኡንጨይ ከሙወን ፔኤስ

. የጓጉለት ቆጮ ተከድኖ (እቃ ውስጥ) ይውላል

.. ያንዳንድ ቀን ሰንበት ካርብ ሮብ ይብሳል

.. የሚውል ሆድ ማለዳ ይርበዋል

770. ቃቻ ደሮይ ሀረ ሽያ ኤሄስ

. ብዙ መደባበስ ሌላ አር ያመጣል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

771. ቃዛለ በ ጡኣ ዴንቱኩሽን ሰንቁለ ጡጋ ማደውሱ

. ቃዘላ (ስም) የራሷን ዋንጫ ማንሳት ሳትችል የሳንቁላን (ስም) ጋን ታግዛለች

.. የራሷ ሲያርባት የሰው ታማስላለች

.. ራስ ሳይጠና ጉተና

.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ

772. ቃድ በይነ ቀምሴ ነጠል በይነን ውሬስ

. እድል የሌለው ቀሚስ ያለ ነጠላ ያልቃል

.. ያልታደለ ከንፈር ሳይሳም ያረጃል

773. ቃድ በይናረ ቃትን ሼምፖይ በይናረ ግሸውሱ

. ቀልብ የሌላት ያማሰለችውን ነፍስ የሌላት ታድላለች

.. እውር እውርን ቢመራ ተያይዞ ገደል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

774. ቃጡዋ በለደ አቱመቴታ ሜንተውሱ

. እንቅስቃሴ አበላሽታ ብልት ትሰብራለች

.. ሲበዛ ማር ይመራል

.. አወቅሽ አወቅሽ ቢሏት የቁስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

775. ቃጡዋ ደርስያረ መጉልያገ ዬለውሱ

. ጨፋሪ ጦር የሚሰብቅ ትወልዳለች

.. ያልዘሩት አይበቅልም

776. ቃጥያጋ ሚሻ ዎጥያጌ ሜስ

. የስስታም ሰው ገንዘብ ነጣቂ ይበላል

.. ስስታም አንድ ያንቀው አንድ የወድቀው

777. ቃጮይ ቶሁዋ ሰጥ ውርሴነን ሀጵያ ክዬስ

. ጉንዳን እግር ነክሶ ሳይጨርስ ራስ ላይ ይወጣል

.. መቼ መጣች ሙሽራ፣ መቼ ቆረጠመች ሽምብራ

.. ፍየል ከመድረሷ ቅጠል መበጠሷ

778. ቁሌ ቁጭን ሻቴ ሜለ አቴስ

. በቆክከር ሲጠርጉ ጣባው ባዶ ይቀራል

.. የቆክከር ቤት ሳይዘጋ ያድራል

779. ቁማ ማይ ቁሩወ

. ምግብ ቁራ በላ

.. ቁቅም ከፈስ ተቆጠረች

780. ቁማጠይ ቁማጣ ዳነው ጌስ

. አንዱ ቆማጣ ሌላውን ጌታው ይላል

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

781. ቁማጠይ ከሊድ ጰክልየን ጉፒስ

. ቆማጣ ሲጠግብ ጓል ላይ ይዘላል

.. እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ወርውሮ ይፈልጋል

782. ቁማጥያ ከለደ ጉሉዋ ቦላን ፕረውሱ

. ቆማጣዋ ስትጠግብ ጓል ላይ ትጨፍራለች

.. አቅሙን አያውቅ

.. እውር ሲቀናጣ ዘንጉን ወርውሮ ይፈልጋል

783. ቁም በይነይ በምበሬ ኮዪስ

. ምግብ ያላገኘ ወጥ ይፈልጋል

.. የምታጠልቀው የሌላት የምትከናነበው አማራት

784. ቁረይኒያ ምንቴነይ በው ዩኪስ

. እስር (ቁርኝት) ያላጠበቀ ሰው ራሱ ያለቅሳል

.. ያልጠረጠረ ተመነጠረ

785. ቁና ቢታን ቁኒ ሄሜቴቴስ

. እጮበጣ አገር ጎብጠው ይራመዲል

.. ወፍ እንደ አገሩ ይጮሃል

.. እንዳገሩ ይናገሩ፣ እንደ ወንዙ ይሻገሩ

786. ቁጠርስያ በር መሬ ላችዮ አየ ኤረውሱ ገውሱ

. የልጅን እንክብካቤ እናት ታውቃለች አለች ጃርት

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

787. ቁፈ ጮሻ ኤሄስ

. ሳል ትውከት ያመጣል

.. የዘፈን ዳር ዳሩ እስክስታ

788. ቅታ ትይን ቅተይ ጎጌስ

. እድፋሙ ቢቀባ እድፍ ይፈሳል

.. ውሃን ቢወቅጡት እምቦጭ

.. አድሮ ቃሪያ፣ ታጥቦ ጭቃ

789. ቅንጠልያ በቅን አይፌ አፉጤስ

. ጆሮ ግንድ ሲያጣፉት አይን ያለቅሳል (ያነባል)

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

790. ቅጥንያየ ደሎላይስ ከንተ ዩከውሱ

. ቂጢኛም ለማህፀን በሽተኛ አምርራ ታለቅሳለች

.. ነግ በኔ

791. ቂ ነአ ግድኮኔ በሉቁዋው ስንታረ ኡቴስ

. ትንሽ ልጅም ቢሆን ባለበቅሎ ከፊት ይቀመጣል

.. ባለፀጋ በሀብቱ ጐልማሳ በሚስቱ

792. ቄረይ ሆኤቶጋ ማናፔ፣ ዎገይ ፖኖጋ ማነ

. ትንሽ ሰው የጠበሰውን ከመብላት ትልቁ የቆነጠረውን መብላት ይሻላል

.. ከትንሽ ሰው ከመበደር ከትልቅ ሰው መለመን ይሻላል

793. ቄረይ ጢጥ አቲድ ጡንዱቂስ

. ትንሽ ሰው ጠብሶ አቅርቦ ይቆነጥራል (ዳር ዳር ይላል)

.. ይሉኝታና ጥቅም አብሮ አይሄድም

.. እንዳይበላ ግፋው እንዳያማህ ጥራው

794. ቄረይ ጢጥንከ ሜነ፣ ሂጥንከ ዝንኤነ

. ትንሽ ሰው ቢጠብሱለትም አይበላም ቢያነጥፉለትም አይተኛም

.. የአህያ ስጋ አልጋ ሲሉት አመድ

795. ቄራ ቁማ ማናፔ ዎጋ ተማ ከሸነ (ሆአነ)

. የትንሽ ሰው ምግብ ከመብላት የትልቅ ሰው እሳት መሞቅ ይሻላል

. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

. ከድኃ ከመበደር ከባለፀጋ መለመን

796. ቁራ ጢጥ ምዝን ዎዘነይ ሚስ

. ትንሽ ሰው ተጠብሶለት በልቶ ያቅረዋል

.. ለናቷ የሌላት አምባር የልጅቷን እጅ ይሰብራል

.. አህያ ማር አይጥማትም

797. ቁራረ ዘትን ገርሳረ አቴስ

. ከትንሽ ሰው ጋር መዋል ያዋርዳል (ዝቅ ያደርጋል)

.. ትንሽ አበላሽ

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው።

798. ቁር ናቱኔ መጣፈይኔ አይቅዶባ ዶጌነ

. ትንሽ ልጅና መጽሐፍ የያዘውን አይለቅም

. ሞኝና ወረቀት የያዘውን አይለቅም

799. ቁር አሰይ መጥንያ ም ጉሴስ

. ትንሽ ሰው ጨው በልቶ ያስቀምጠዋል

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

.. ትንሽ አበላሽ

800. ቁር ዎራን ሆተይ ዴኤስ

. ከትንሽ ጫካ ውስጥ መለሎ የማገር እንጨት ይገኛል

.. ምንም ብቀጥን ጠጅ ነኝ

.. ቀጥኜ ቢያየኝ ጅማት ለመነኝ

801. ቁር ዱሬ ነሽ ነሽ ዮትቴ ጌስ

. ትንሽ ሀብት ያለው አሞግሱኝ ይላል

.. ትንሽ ያላት እንቅልፍ የላት

802. ቄስያ መጫስያ ኤራ ደረይስ ጋደ መጣፋ ሚጨውሱ

. የቄስ ሚስት አወቅሁ ብላ መጽሐፍ ታጥባለች

.. አወቅሽ ቢሏት የቄስ ሚስት መጽሐፍ አጠበች

803. ቄሴ ዱቶዋ በይዚስ

. ቄስ መቃብር ይሸጣል

.. መሸጥ የለመደ እናቱን ያስማማል

804. ቆልኦ ሙሰይ ቆርየው ሎኦሽን ቆሙወው ኢተ

. እጓዳ መብላት ለጉረሮ (ለሰውነት) ጥሩ ነው ግን ለስም ጥሩ አይደለም።

.. ሆዱን የወደደ ማዕረጉን ይጠላል

805. ቆልኦን ሚጭያ ጌለኣያ ውይግየን ሼኔተውሱ

. ጓዳ የምትሰቅ ልጃገረድ ሳሎን ስታልፍ ትጠየፋለች

.. አስመሳይ

.. ሞኝ አያውቁብኝም ባይ

806. ቆልኦን ሽይያረ ውይጌን ጮይያሮ ኪታ ሞሮፐ ገውሱ

. ጓዳ የምታራ ሳሎን የምታስታውከውን ቤቱን አታበላሺ ትላለች

.. ዝንጀሮ የቂጧን መላጣ ሳታይ በልጇ ትስቃለች

807. ቆልኦን ጉስያረ ፔንጌን ጮይያሮ ሚጨውሱ

. ጓዳ የምትቀዝን ደጃፍ በምታስታውከዋ ላይ ትስቃለች

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

808. ቆማጣይ ቆማጣ ጎዶ ጌስ

. ቆማጣ ቆማጣን ጌታው ይላል

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

.. እርስ በርሱ ስጋን በኩበት ጠበሱ

809. ቆሞ ግን ሙጦ አሾይ ግዴስ

. የራስ (ድርሻህ) ከተባለ ምትር ስጋ ይበቃል

.. የሰጡህን አትንሳ ያደረጉልህን አትርሳ

.. ለስሚ መጠሪያ ቁና ሰፋች

810. ቆሞረ ኡይየ ጋሞይ ጠዴረ ኡይየ ጋራ ሃታ ኔ ተው ሞረነ ጌስ

. ከላይ የሚጠጣ አንበሳ ከታች የሚጠጣውን ድኩላ ውሃ አታደፍርስብኝ ይላል

.. አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ

811. ቆሞን ሉጐንተሶ አይያ ኩቱወ ዋጠደ ጎየውሱ

. እላይ ሰፈር የነሱን እናት ዶሮ ጠምዳ ታርሳለች

.. የማይሆን ነገር ለሚስትህ አትንገራት

812. ቆሞይ ጠየናፔ ቆሬ ዱጦ ጌስ ቃጮይ

. ስም ከሚጠፋ አንገት ይበጠስ ይላል ጉንዳን

.. ስም ይበልጣል ከስር

813. ቆሞይ ጉጠናፔ ቆሬ ዱጦ ያጌስ ቃጮይ

. ስም ከሚጎድፍ አንገት ይበጠስ ይላል ጉንዳን

.. ስም ይበልጣል ከስር

.. ስም ከመቃብር በላይ ይውላል

814. ቆረተ ቆሞተውሱ ዬሎ ነአ መድገውሱ

. ቡዳ ዘር ቆጥራ የወለደችውን ትበላለች

.. የዘሬን ብተው ያንዘርዝረኝ

.. ዘር ከልጓም ይስባል

815. ቆርቆሮ ሌቀይ ማታ ዎሴስ

. ቆርቆሮ የናቀ ሳር ከዳን ይለምናል

.. የቀበጡ ዕለት አይገኝም ሞት

.. ሲስሚት ትታ ሲስቢት

816. ቆርያ ቀንጥን ሽየይ ቤትዮ ሙጫ

. አንገቱ ቢቆረጥ አር የሚታይበት ቆራጣ (ድዊ)

.. አጭር አህያ ሁል ጊዜ ውርንጭላ

.. አጭር ሰው አንቱ ሳይባል ያረጃል

817. ቆርያ ጨላጋ አይፍየን ብረድያ ዬዳጌ ዬድሴስ

. አንገት ያነቀውን አይን መጠንቆል ያስለቅቃል

.. የጉረሮን መታነቅ የአይን መደንቆል ያስጥለዋል

818. ቆሬ ቦርኮተ ዱፐይ ሰሌነ

. አንገት ትራስ ስንደዶ ምንጣፍ ነው

.. የድሃ ነገር አያምር

.. የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም

819. ቆሴቶ ዎረይ ኬስ ቤሴስ

. የተደበቁበት ጫካ ገልጦ ያሳያል

.. ቀን ሲጎድል...

.. ጊዜ ነው እንጂ ቁም ነገራም የሰው ልጅነት አያኮራም

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

820. ቆቅያ ነእያ አዋ ግሻረ ጤለውሱ

. የእውር ልጅ ያባቷን ጭምር ታያለች

.. ረዥም ጦር ባይወጉበት ያስፈራሩበት

.. አባት መኩሪያ ወንድም ጋሻ

821. ቆቅደ አይፌ ፐጥድ ሜድደ ጦሳ ጨዬስ

. የታወረ አይን ሲበራ የፈጠረውን አምላክ ይሰድባል

.. አይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች

.. ታሞ የተነሳ እግዜርን ረሳ

822. ቆቄ መጣፈን ዴእየ ኡበይ በሱንታ ጌስ

. መጽሐፍ ውስጥ ያለው ሁሉ የኔ ስም ነው ይላል እውር

.. ቡልጋ ጤፍ ቢወቃ አዲስ አበባ ያለው አይኔ ውስጥ እብቅ ገባ አለ አሉ

.. እውር ምን አይቶ ደንቆሮ ምን ሰምቶ

823. ቆቄ ሽተይ ደርኮ አድጽ ሀጌ አወ ባዘ ጌስ

. ሽታዬ የተባለው እውር ወደ ጓሮ አልፎ ይሽ የትኛው ደን ነው ይላል

.. እውር ቢሸፍት ከጓሮ አያልፍም

824. ቆቄ ሾላ ሌቄስ

. እውር ሸውራራን ይንቃል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

825. ቆቄ ቆቅያ ጎቺድ አፉዋን ጌሌስ

. እውር እውርን ሲጎትት ገደል ይገባል

.. እውር ለእውር ተያይዞ ገደል

826. ቆቄ በ ናቱፔ ጌመይስ ጊድ ሰዎ ማታ ግዶን ፔኤስ

. እውር ከልጆቼ ተሰወርኩ ብሎ ጠጅ ሳር ውስጥ ይውላል

.. አልሸሹም ዘወር አሉ

.. ዕውር ቢሸፍት እስከ ጓሮ

827. ቆቄ ቢታን እስ አይፌ ጎደይ ከዎ

. በእውሮች አገር አንድ አይናማው ንጉስ ነው

.. በቆማጣ ቤት አንድ ጣት ብርቅ ነው

.. አንድ ያላት ዕንቅልፍ የላትም

828. ቆቄ ኩሳሞ ኤሬነ

. እውር ጨብራሬን አያውቅም

.. ያንዱ ችግር ለሌላው የእንጀራ ልጅ ነው

.. ያልተነካ ግልግል ያውቃል

829. ቆቄ ጎችያ ነአ ወጲስ

. እውር መሪውን ይደበድባል

.. እውር ሲቀናጣ ምርኩዙን ወርውሮ ይፈልጋል

830. ቆትድ ዜርን ሞክድ ቤቴስ

. ደብቀው ቢዘሩ በቅሎ ይታያል

.. ግመል ሰርቆ አጎንብሶ መሄድ

.. ተደብቃ ትፀንሳለች ሰው ሰብስባ ትወልዳለች

831. ቆትዶሮ ዎትዳጌ ዴሜስ

. የተደበቀውን ያው የደበቀው (ደባቂው) ያገኛል

.. ካለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

832. ቆዳ ደሮይ ቦሎቴፔ በይረ ኦቴስ

. እድሜን መቁጠር ሲበዛ ከአማት ታላቅ ያደርጋል

.. አጥብቆ ጠያቂ የናቱን ሞት ይረዳል

.. ዶሮ ሲጭር ማረጃውን ያወጣል

833. ቆጩ ግየ ባጭራይ ቆስንከ ፔኤነ

. የሚጣፍጥ የቆጮ ምግብ ቢደብቱት አይውልም

.. ቆንጆና እሸት አይታለፍም

.. የፍየል አይን ከጎመን የነብር አይን ከፍየል

834. ቆፈይ በይነ ቆሬ ኡስታ ውርሴስ

. ሀሳብ የሌለው ጉረሮ መበያ ይጨርሳል

.. ሞኝ የዕለቱን ብልጥ የዓመቱን

.. ሆድ ለማታ በልቶ ለጧት

835. ቆፈይ አሩስያ ሚዛ ሄሚድ ፒእዮ ዎዴ፣ ዎልቀይ ቆነሽያ ቀሹዋ ቶክ ዴንቴነ

. ልብ (ሐሳብ) የአሩሲ ክብት አግዶ ሲያውል ጉልበት (አቅም) የደረቀ ኮባ ቅጠል መሸከም ያቅተዋል

.. ማውራትና መስራት ለየቅል

.. ምኞትና የህልም ጉዞ መድረሻ የለውም

836. ቆፐይ ዲሽን ቆፔቲቤናጌ ኤኪስ

. የታሰበለት (የተመኙለት) እያለ ያልታሰበ ወሰደ

.. መታደል ነው እንጂ አይታገሉም

.. ይታደሉታል እንጂ አይታገሉም

837. ቆፔነን ጉፕደይ አይቂነ ሶሁዋፔ ሜኤስ

. ሳያስብ የዘለለ ከማይጠገንበት ቦታ ላይ ይሰበራል

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. ሳይሰራ ያመረተ ሳያውቅ የተረተ

838. ቆፔነይ ሙጢነን ሜስ ጌቲስ

. የማያስብ ሳይመትር ይበላል (ይውጣል)

.. ሃሳብ የሌለው ማደሪያ አይቸግረውም

## በ

839. በ ሼምፑወው ዎጠይሱ፣ ፒንጌን ጎተረውሱ

. ለነፍሷ ትሮጣለች፣ በራፍ ላይ ታጓራለች

.. ሳይቸግር ጤፍ ብድር

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

840. በ በይራ ቦንቺነይ አሰ በይራስ ሀድያ ቶኪስ

. የገዛ ታላቅ ወንድሙን የማያከብር የሌላውን ታላቅ ወንድም ሱሪ ይሸከማል

.. አባቱን ሳይመስል የተወለደ ልጅ ጐረቤት ያሳማል

841. በ ቦላ ተማ ፕትድ በነአ ቦላ ተማ ፕቲቲስ

. ራሱ ላይ ያለውን እሳት ጠርጐ በልጅ ላይ ያለውን እሳት ይጠርጋል

.. ከራስ በላይ ንፋስ

842. በ ቱማፔ አጌነይ በር ቱማፔ ምዚነይ አሳረ ዬኤነ

. እውነቱን እያወቀ ያልተወ ከራሱ ሰውን ያላበላ ከሰው ጋር አይኖርም

.. አውቆ መተው ነገሬን ከተተው

.. ኑር ከአገር ሂድ ካገር

843. በ ቴሉዋ ከሜነ ጌሌሾይ በ ነአጋ ጤልድ ሚጩስ

. የራሱን መላጣ የማይሸፍን ዝንገሮ የልጁን አይቶ ይስቃል

.. ዝንጀሮ የራሷን መላጣ ሳታይ የልጇን አይታ ትስቃለች

844. በለኮይ ዎድያ ኡቴስ

. ዲቃላ ጊዜውን (ቀኑን) ያሳልፋል

.. ቀን እስከሚወጣ ያባቴ ገበሬ ያግባኝ

845. በለይ በይነ ምሽርያ በለኩዋ ዬለውሱ

. ተንኰል (ክፋት) የሌለባት ሴት ዲቃላ ትወልዳለች

.. ለኃጥአን የመጣ ለጻድቃን ይተርፋል

846. በለይ ኑሶጋ ባወ ዮፐ ግየጌ

. ስህተቱ የኛቤት ነው፣ የለም አትምጪ የሚል

.. የአፍ ወለምታ በቅቤ አይታሽም

847. በሉቁወይ ሱቅን ጩርቃወይ መላቴቲስ

. ባለበቅሎው ቢፈሳ በባለጨርቅ ላይ ያመለክቷል (ይጠነቁሏል)

.. አህያውን ፈርቶ ዳውላውን

.. የእምዬን እከክ ወደአብዬ ልክክ

848. በሉቅያ ቀኮጋፔ ፐንዶረ ኢተ

. በቅሎዋ ከመርገጥዋ ፋንዲያ መጣልዋ (በፋንዲያ ማበላሸትዋ) ይከፋል

.. አህያ ከመሞትዋ መጮተትዋ

849. በሉቅያ በ ጠለለው በ ጎደ ቀከውሱ

. በቅሎዋ ሲደክማት ባለቤቷን ትረግጣለች

.. ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው

850. በሉቅያ ኑሶሮ ጊሽን ቀከውሱ

. በቅሎዋ የኛ ቤት ናት ስትባል ትረግጣለች

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

851. በሉቅያ ዎዶሩዋ ዱተውሱ ግን በው ቃንተውሱ ጌቴስ

. በቅሎ ገመድ በጠሰች ቢባል ለራሷ አሳጠረች ይላል

.. በቅሎ ገመድ በጠሰች ቢሉ ለራሷ አሳጠረች አለ

.. አተርፍ ባይ ጎዳይ

852. በሉቆይ ሰጋርያ ጊግሰደ ፕሪጠነ ጊድ ኡበ አቴስ

. በቅሎ ስግሪያው፣ አስተካክሎ እጋልባለሁ ሲል ጠቅላላውን ይቀራል

.. ያመነታ ተመታ

.. ጊዜ ያለው ጊዜ አይጠብቅም

853. በሉቆይኔ ሀሬነ ቀኪት አቸ ሚንቲቶኮነ

. በቅሎና አህያ ተራግጠው ጥርስ አይሳበሩም

.. አህያ ላህያ ቢራገጥ ጥርስ አይሳበርም

854. በልድ አቤቱስ – ዎርድ አሌቁቱስ

. ሲያጠፋ ይቅርታ ይላል – ገድሎ ይሸለማል

.. ያደፈውን በእንዶድ፣ የጐለደፈውን በሞረድ

855. በልጉዋ አትድ ከና ሱሌስ

. ክረምትን አሳልፎ ውሻ ይሰቅላል

.. ጅብ ከሄደ ውሻ ጮኸ

856. በልገ ሻኾደ ኪታ ቦኔ ጡጊስ

. ክረምት ያከረመውን ቤት በበጋ ያቃጥላል

.. ያሳደግኋት ጥጃ አለችን በርግጫ

.. አይነጋ መስሏት ቋት ላይ አራች

.. ባጐረስኩት እጇን ተነከሰኩ

857. በልገ ተማ ሆእየይ ቦኔ አዋ ሆኤስ

. የክረምት እሳት የሚሞቅ የበጋንም ዐሐይ ይሞቃል

.. ሞኝ ሰኔ በጋው ነው

858. በልገ ኪስየ ቁርሴ፣ ጥደኃ ኪሲየ ዎልቃ አው ኤሬስ

. ክረምት የሚያወጣ ቁርስና ዳገት የሚያወጣ ጉልበት ባለቤቱ ያውቃል

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

859. በራተነው ባብረከ

. እንዲህ የምታንቋልጪው ለመክረም አይደለም

.. የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታውቃል

.. የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት

860. በር መለ ከፎይ በር መለ ምተን ኡቴስ

. የማይሆን ወፍ በማይረባ ዛፍ ላይ ያርፋል

.. ግም ለግም አብረህ አዝግም

861. በር መሬ ላቻ ጌንእያ ኣያ ኤረውሱ

. የልጅዋን አላላስ እናት ሚዳቋ ራሱዋ ታውቃለች

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. እናት ለልጅዋ ነቢይ ናት

862. በር ቦሉዋስ እፍታ እምድ ጐደርየን ሚቴቴስ

. ለአማቹ መዝጊያውን ሰጥቶ ለራሱ በጅብ ይበላል

.. ይሉኝታና ጥቅም አብሮ አይሄድም

.. ሞኝ ለጋስ ራቱን ለሰው ሰጥቶ ራሱ ጦሙን ያድራል

863. በር ነኣ አሃ በእድ በጎዳ ነኣ ሀርግያጋ ቤአነ ቤስ

. የራሱን ልጅ አስከሬን አዝሎ የታመመውን የሹም ልጅ ለመጠየቅ ይሄዳል

.. የበላይ አደባይ

.. ለተሾመ ይሟገቱለታል በተሻረ ይመሰክሩበታል

864. በር ኣዋ ቤኤነይ ሄዘንተን ጫቁስ

. አባቱን ያላየ በሦስተኛው (አያቱ) ይምላል

.. አባቱን የማያውቅ በአያቱ ይምላል

.. በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት ፈረስ አያቴ ነው ይላል

865. በር ገዴን ድንክየን ዩኪትየ ኡዱንጥያ አሰ ዴሬን በቅን ሀይቀውሱ

. ባገሯ በክብር የሚለቀስላት ዝንብ እሰው አገር በጥፊ ተመታ ትሞታለች

.. ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢቀመጡት ፈረስ

866. በርሱዋ ሚዛተ መጫስያ በቀው ኤፍን ሀንገውሱ

. ጉርሻ የለመደች ሴት በጥፊ ሊመታት እጅ ሲያነሳ አፏን ትከፍታለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

867. በርሱዋ ሚዛተ መጫስያ በቀው ኩሽያ ዴንትን ዶና ሀንገውሱ

. ጉርሻ የለመደች ሴት በጥፊ ሊመታት እጅን ሲያነሳ አፏን ትከፍታለች

.. የለመደች ጦጣ ሁል ጊዜ ሽምጠጣ

868. በርስ ምዮብ ባወሽን ነኤ ነኣ ድቸነ ኤፈውሱ

. ለራሷ የምትበላው ሳይኖራት የልጇን ልጅ ልታሳድግ ታመጣለች

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

869. በርስ አቅዮሰይ በይነ ሃተይ ምታ ቶኪ ዩዬስ

. ለራሱ ማደሪያ የሌለው ውሃ እንጨት ተሸክሞ ይዞራል

.. አባይ ማረፊያ የለውም ግንድ ይዞ ይዞራል

870. በርስዶ ኩሼ ዛር ጨዬስ

. ያጐረሱት እጅ መልሶ ይወጋል

.. ባጐረስኩ እጄን ተነከስኩ

.. ብር ላበደረ ጠጠር

871. በርሶ ነኣ ሀይቅዳጋ በአደ በጎዳሶ ሀርግዳጋ ቤአነ በውሰ

. የቤቷ ልጅ የሞተውን አገላ ጌታዋ ቤት የታመመውን ለመጠየቅ ትሄዳለች

.. የበላይ አደባይ

.. የድሃ ነገር ማንገቻ የለውም

872. በርሶ አዘላ ዎትድ አሰሶ ቀራ ቦሬስ

. እቤቱ ሰነፍ አስቅምጦ የሰውን ቤት ቀልጣፋ ይሳደባል

.. ያሉሽን በለማሽ ገበያም ባልወጣሽ

873. በርሶን ባርዮብ በይናጌ አሰሶ በጋ ካሬስ

. እቤቱ የሚጐረስ ሽራፊ የሌለው የሰውን ቤት ግማሽ ይንቃል

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

874. በርበርያ መላተይ ቁፈ፣ ሙጀልያ ቶሆይ የበቻ

. የበርበሬ ምልክት ሳል ነው፣ ሙጃሌ የበላው እግር ጠማማ ነው

.. እንዲያው በመላ ፈስ ዳለቻ ነው

875. በርነን ፓጭድ ፕቶ ግዶን ኮዬስ

. በራሱ ታገቦ ጥራጊ ውስጥ ይፈልጋል

.. ሌባ እናት ልጇን አታምንም

876. በነከ አሰ ጊድ ተ አወይ ሱሬ ግጥድ ግያ ቤስ

. ራሱን ከሰው ቆጥሮ የኔ አባት ሱሪ ታጥቆ ገበያ ይሄዳል

.. ቁቅም ከፈስ ተቆጠረች

.. ሰው መሳይ በሸንጐ

877. በርካ ቆፕደይ ዝንኤነን አቅን አሳረ ቆፕደይ ዝንእ አቄስ

. ብቻውን ያሰበ ሳይተኛ ሲያድር ከሰው ጋር ያሰበ ተኝቶ ያድራል

.. ካንድ ብርቱ ሁለት መድሃኒቱ

.. አንድ በሬ አርሶ አንድ ሰው አስቦ

878. በርዮ በየነ ሃተይ ከና ሚስ

. ለራሱ የሚደርቅ ወንገ ውሻ ይበላል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

879. በርዮ በየነ ባቄልያ ኮክን እጠደ ሻይን ከጠውሱ

. ለራሷ የምትጠፋ ባቄላ ቀቅለዋት እምቢ ብላ ተቆልታ ትበስላለች

.. ላታመልጪኝ አታሩጪኝ

880. በርዮ በይናረ ከዎ ግያ ጤሰደ ጪየውሱ

. ምንም የሌላት የንጉስን ገበያ ጠርታ ትረግማለች

.. ያጣ ወሬ ነው

881. በርዮ በይናጌ ላጡን በሱዋ ሜስ

. ምንም የሌለው ሰባት ቁራሽ ቂጣ ይበላል

.. እንኳን የሸመተ ያረሰም አይችልህ

882. በርዮ ባርዮጌ በይናጌ በጋ ከሬስ

. የሚጐርሰው የሌለው ግማሽ ይንቃል

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

883. በርዮ ዞልያ መውሽን ናቱ ናታ ድቸነው ኤሀውሱ

. ለራሷ ወቄት ትበላለች የልጇን ልጅ ልታሳድግ ታመጣለች

.. አባይ ማረፊያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

884. በርዮ ጌለትድ አሰ ኢተ ጌስ

. ለራሱ ጠምሞ ሰውን ክፉ ይላል

.. የአብዬን እከክ ወደእምዬ ልክከ

885. በሱዋ ሆኤተ ግን በይረው መገና በውሱ

. ቁራሽ ቂጣ አሙቁልኝ ቢላት ለስሞታ ሄደች

.. ባለጌ ልጅ ሲቆጡት ያለቅሳል

886. በሶ ሜናጌ አሰ ሶን በጋ እምን ቢሌቴስ

. ቁራሽ በልቶ የማያውቅ እሰው ቤት ግማሽ ተሰጥቶት ያኮርፋል

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

.. ጅብ እማያቁበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

887. በሶን ሰሌንን ዝንእያረ አሰሶ ባደ ፕራሽያ ዬገ ገውሱ

. እቤቷ ሰሌን ላይ የምትተኛ እሰው ቤት ሄዳ ፍራሽ አንጥፉልኝ ትላለች

.. ጅብ እማያውቅበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል

888. በሼ ቁመይ ጩቸ ጠላለ

. የዝርክርክ ምግብ ቅማል ብቻ ነው

.. ከአያያዝ ይቆረጣል፣ ከአነጋገር ይፈረዳል

889. በሼስ ጊሽን ኤጩርያ በውሱ

. ለምጣድ ሲባል አይጥ ትሄዳለች (ታመልጣለች)

.. ሁለት ወዶ አይሆንም

.. በሰበቡ መምሬ ተሳቡ

890. በቀ ኩሼ በልን በቁተ ሽየይ ኤሬስ

. በጥፊ የመታ እጅ ሲረሳ የተመታ ጆሮ ግንድ አይረሳም

. የመታ እጅ ቢረሳ የተመታ ጆሮ ግንድ አይረሳም

.. የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ

891. በቅ ሸሞይኔ በነክ ዬሉይኔ እሱዋ

. አይተው መዝነው የገዙትና አምጠው የወለዱት አንድ ናቸው

.. ያለባለቤቱ አይነድም እሳቱ

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

892. በቅ ባሬስ ጎደሬ

.. ተሯሩጦ ይበላል ጅብ

.. መቀመጥ መቆመጥ ነው

.. ያልተገላበጠ ያራል

893. በቁታጌ ኤሬስፔአትን በቀይ ኤረነ

. በጥፊ የተመታ ያውቃል እንጂ የመታ አያውቅም

.. የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳ

894. በቁትያ ጌዴ አጉንታ መጤስ

. የሚቅበዘበዝ እግር እሾህ ይለቅማል (እሾህ ውስጥ ይገባል)

.. አለማረፍ ጣር ይበዛል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትመጣለች

.. አለማረፍ የተርብ ቤት መቀስቀስ

895. በበንታ ዬሁዋ ቦክ ዬከኔ ዬክ ቦከኔ?

. የድብን ለቅሶ ቆፍረን እናልቅስ ወይስ አልቅሰን እንቆፍር

.. አይዋጥ አይተፋ መላው የጠፋ

896. በበው ጎደሬ አሰበው ዮቁ ጌስ

. በራሱ ይቆጣል የሰውን ይከጅላል

.. የራሷ ጊዜ አለቀሰች የሰው ጊዜ ሳቀች

.. እንካን የማያውቅ አምጣን ማን አስተማረው

897. በባ በሸበይ አሰ በሶ በሼስ

. የራሱን ያበላሸ የሰውን እንጀራ ያበላሻል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

898. በባን ካእን ባውስ ዬክን ድግየይ ባ

. በራሱ የሚጫወተውንና ለአባቱ የሚያለቅሰውን የሚከለክል የለም

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

899. በባን ካእየኔ ባወን ጨቅየባኔ ድጌቴነ

. በራሱ ንብረት የሚጫወተውንና ባባቱ የሚፎክረውን ከልካይ የለውም

.. ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው

.. ለራሱ የሚበጀውን ባለቤቱ ያውቃል

900. በታልያ ምተይ ምተ ጊድ ብን ማታ ክዬስ፣ ማታ ጊድ በጫረ ብን ቢተ ክዬስ

. የባተሊያ እንጨት እንጨት ነው ብለው ሲመጡ ሳር ይሆናል፤ ሳር ነው ብለው ማጭድ ይዘው ሲሄዱ አፈር ይሆናል

.. ወፍ ነሽ እዩት ጥርሴን አይጥ ነሽ እዩት ክንፌን

901. በቶይ ዴእሽን ቃዶይ ሜስ

. የቆረሱለት እያለ የታደለ ይበላል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

.. አትሩጥ አንጋጥ

902. በነ ሰበይኔ ጩርቀ ስከይኔ እሱዋ

. ራሱን የሚያሞግስና ቡትቶ የሚሰሩ አንድ ነው

.. እዩኝ እዩኝ ያለች ደብቁኝ ትላለች

903. በነ ቆፐይ በ ፑራ ቡልእ ላሌስ

. ራሱን (ችግሩን) ያሰበ የሆዱን ህመም በስራ ያጠፋዋል

.. ድሃ ካልሰራ ዶሮ ካልጫረ

904. በነ ቤኤናረ በ ለግያ ሚጨውሱ

. የራሷን ያላየች የጓደኛዋን አይታ ትስቃለች

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. ያሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

905. በነ ቤኤነይ በጎዳ ቦሬስ

. ራሱን ያላየ ጌታውን ይነቅፋል

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

906. በነ ነሸይኔ ጩርቀ ደንጨይ እሱዋ

. ራሱን የሚያሞግስና ጩርቅ የሚያሸርጥ አንድ ነው

.. እዩኝ ያለች ደብቁኝ ትላለች

907. በነ ኤረይ አሰ ባዶ በሼስ ጌቴስ

. ራሱን ያወቀ የሌላውን ድራሽ ያጠፋል

.. ከራስ በላይ ንፋስ

.. ራሱን የማያውቅ ጌታውን አያውቅም

908. በነ ከሚነ ቁፍያ ሙቅያ ዛላ ከመውሱ

. ቢራቢሮ ለራሷ የማይበቃትን ክንፍ ንጣፍ ድንጋይ ታለብሳለች

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

909. በነ ዎርየ ጡፍያ አዴ ቁሊቶፔ ቶክድ ዩስ

. ራሱን የሚያስገድል ጽሑፍ ሰውየው ከቁሊቶ ተሸክሞ ይዞ ይመጣል

.. የማያውቅ የናቱን ተገኳር እንደሰርግ ይቆጥራል

.. ያላወቁ አለቁ

910. በነን ቤአይ መላትድ ጎዚስ

. በራሱ ያየ በምልክት ይሸብባል (ይከድናል)

.. ሌባ እናት ልጇን አታምንም

.. ሲሰርቅ ያየሁትን ቢሰጠኝ አላምነውም

.. ያየ ይናገራል፤ የተወለደ ይወርሳል

911. በነን ቤአይ ፕቱውን ኮዩስ

. በራሱ ያየ ጥራጊ ውስጥ ይፈልጋል

.. ሌባ እናት ልጇን አታምንም

912. በነን ቤእደይ ፕቱወን ኮዩስ

. በራሱ ያየ ጥራጊ ውስጥ ይፈልጋል

.. ሌባ እናት ልጇን አታምንም

913. በንካው ጉለሻዎ ከንት ዩኪስ

. የአባላዘር በሽተኛ ለማህፀን በሽተኛ አምርሮ ያለቅሳል

.. ነግ በኔ

.. አፍንጫ ሲመታ አይን ያለቅሳል

914. በንጋ ላለደ መቃ ጋቡልየ አኖ ነአው ኔ በንጋይ በራቶ

. ገብስ በትነህ አገዳ በሶ የምትሰራ የአኖ ልጅ ገብስህ ይበርክት

.. ሞኝ ከመውለድ ማስወረድ

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

915. በኡወን ኤዩትዶ ቡኩሎይ ድሹወን ሜቱስ
. እያዘሉ ያሞላቀቁት (ያባለጉት) ቡኩሎ ለማሳደግ ያስቸግራል
.. ያልተገራ ፈረስ ይጥላል በደንደስ
.. ያልተቀጣ ልጅ ቢቆጡት ያለቅሳል
916. በኡዋ ዴሸይ ዱልያ ዴሽሲስ
. ጠማማ አሸካከም ቂጥ ያጣምማል
.. ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል
917. በከነይ ባወሽን ጎደሬ አሾ ሜነን አቅኪ ጌስ
. ቤሳ የሌለው ጅብ ስጋ ሳልበላ አላድርም ይላል
.. ራት የሌላት ምሳ አማራት
918. በከንያ ባወሽን አርሰይ ሰሌና ገውሱ
. ቤሳ የሌላት አልጋው ሰለን ነው ትላለች
.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል
919. በካሎ ለይተን ባደ ሜንትያ ዩለውሱ
. በበካሉ ዘመን በደ መንታ ትወልዳለች
.. እቤት ዶሮ ሲታረድ ከዱር ቆቅ ይያዛል
920. በው ቀሾፔ ክዩናጌ አሰስ ዋሴ ጌሌስ
. ለራሱ ከእስራት ያልወጣ ለሰው ዋስ ይሆናል
.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ
921. በው ቀጠራ ጌሌነይ አሰ አይፍያ ኦይቄስ
. ለራሱ ያልተገረዘ የሰውን አይን ይይዛል
.. አንቃ ለራሱ አይበቃ ለሰው ጠበቃ
.. የሚሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ
922. በው በለደ ጡመን ሄሚቱውሱ
. ራሷ ቀውሳ በጨለማ ትሄዳለች
.. እብድ የያዘው መልከ አይበረከትም

923. በው በለደ ጡመን ሄሚተደ ተነ አዘቀ መውሱ ገውሱ

. ራሷ ቀውሳ በጨለማ ሄዳ ጭራቅ በላኝ ትላለች

.. ሞጭሚጫ በስንጥር ያሳበባል

.. የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ

924. በው በልድ በንጋ ናት በለ ጌስ

. ለራሱ ተሳስቶ የባንጋ ልጆች ክፉ ናቸው ይላል

.. የአብዬን እከክ ወደ እምዬ ልከክ

925. በወ በልድ በንገ ነአንተሶ በለ ጌቴስ

. ራሱ አጥፍቶ የነባንጋ ቤተሰብ ክፉ ናቸው ይላል

.. የአብዬን እከክ ወደ እምዬ ልከክ

926. በው በይነይ ባው ጉወቻ ጌሌስ

. መኖሪያ ቤት የሌለው ከአባቱ አሽከር ይጠጋል

.. ቀን እስኪያልፍ ያባትህ ባሪያ ይግዛህ

927. በው በይነይ ከዎ ግያ ጨዬስ

. ለራሱ የሌለው የንጉስ ገበያ ይሳደባል

.. ያጣ ወሬ ነው

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

928. በው በይናረ ጵንያረ ገነውሱ

. ለራሷ የሌላት የሰውን በቱፌ ትጠጣለች

.. ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል

929. በው በይናጌ ዞኮይ ዱጢን ገኔስ

. የሌለው ጀርባው እስኪበጠስ ይጋተራል፣ (ይጠጣል)

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

930. በው በይየ ሃተይ ኡሰን ሸምዶ ኤሳ ኤክዲ ጠዬስ

. ለራሱ የሚጠፋው ውሃ በጊደር የተገዛ ማር ይዞ ይጠፋል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

.. ሊያልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ

931. በው በይየ በይኪ ከርያ ናግየ ካይግ ኤክድ በዩስ

. ለራሱ የሚጠፋ ሃጅ ደጅ የሚጠብቅ አዛውንት ይዞ ይጠፋል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

.. በጥባጭ ካለ ጥሩ ውሃ አይጠጣም

932. በው በይያሬ ጵንየረ ገንያሬ

. ለራስሽ የምትጠሬ በቱፈ የምትጠጪ

.. የሚያልፍ ቀን የሚያልፍ ስም ይሰጣል

933. በው ቡከደ በው ሾከደ ኡየውሱ

. ለራሷ ንጣ ለራሷ ለቅልቃ ትጠጣለች

.. ስሱ አንዱ ያንቀው አንዱ ይወድቀው

934. በው ብየ ባጩ ከርያ ናግየ ከና ኤክድ ቤስ

. ለራሱ የሚሄድ ባጩ ደጅ የሚጠብቀውን ውሻ ይዞ ይሄዳል

.. የሚያልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ

935. በው ብየ ጋብ ከርያ ናግየ ከበ ኤክ ቤስ

. ለራሱ የሚሄድ ጋቤ ደጅ የሚጠብቀውን ከሲታ ውሻ ይዞ ይሄዳል

.. የሚያልፍ ውኃ አደረገኝ ድሃ

.. ምቀኛ የወደቁ እንደሆነ የሞቱ ይመስለዋል

936. በው አይኔ በይናጌ በ ጎዳ በሉቁወው አሞሊያ ሸሚስ

. ለራሱ ምንም የሌለው ለጌታው በቅሎ አሞሌ ይገዛል

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

937. በው አይኮ በይናጌ አሰባ ከሬስ

. ለራሱ ምንም የሌለው የሰውን ይንቃል

.. አህያ የሌለው በቅሎ ይንቃል

938. በው ከልደይ አግየን ጉፔስ

. የጠገበ ሰው በየመንገዱ ይዘላል

.. የጠገበ ሰው ራሱን አያውቅም

939. በው ከልዳጌ ሽያ ቦል ኡቲድ ሱይቴስ

. የጠገበ ሰው አር ላይ ተቀምጦ ያፏጫል

.. የጠገበ አበደ

940. በው ኬሆ ጊድ ባው ጉአቻ ጌሉቲስ

. ለራስ ይበጅ ተብሎ ያባት አገልጋይ ያገቧል

.. ቀን እስኪያልፍ ያባትህ አገልጋይ ይግዛህ

.. ቀን ያልፋል እስኪያልፍ ያለፋል

941. በው ኬት በይናጌ በ ጎዳ ነአ ዱልያ ዩሬስ

. ለራሱ ቤት የሌለው የጌታውን ልጅ ቂጥ ይስማል (ያታልላል)

.. ሮቃ የገዘሆን አለቃ ለምሳር አይበቃ

.. ለቂጡ ጨርቅ የሌለው ቆንጆ ያባብላል

942. በው ፐጤነ ኡሪይ ከና ላፑና ሃሬስ

. ለራሱ የማይጠረቃ ሰባት ውሻ ያሳድጋል

.. አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

943. በው ፐጤነይ ከና ላፑና ድቼስ

. ለራሱ የማይጠረቃ ሰባት ውሻ ያሳድጋል

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

944. በውታ ምዮሺኔን አቶ ኩሜታ

. በክት ከበሉ እንስራ ሙሉ

.. ከለገሱ አይቀር ይንጋለሉ

.. ያበጠው ይፈንዳ

945. በውኢ በውእደ ተመይ ሴፋረ ሜስ

. ግው ያለ እሳት ከቆጥ ጭምር ያቃጥላል

.. ትዕግስት ፍርሃት አይደለም

.. የተዳፈነ እሳት

946. በየ ፐረይ ዴእሽን ኮይየ ፐረይ ደፉሬስ

. የጠፉ ፈረስ እያለ የሚፈልገው ፈረስ ይደክማል

. ጠፍቶ የሚፈለግ ፈረስ እያለ ለፍለጋ የወጣው ፈረስ ይደክማል

.. የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ

947. በየነ ሃተይ ከና ሜስ

. የሚደርቅ ውሃ ውሻ ይበላል

.. ሲያልቅ አያምር

.. ውሃ ሊያንስ ሲል ይገማል ሰው ሊያንስ ሲል ይኮራል

948. በየነ ሚሸይ ደንጨዋፔ በዩስ

. የሚጠፉ ገንዘብ ከመቀነት ይጠፉል

.. የሚፈርስ ከተማ ነጋሪት ቢመታ አይሰማም

.. አይጣል ነው

949. በየነ ጊደበይ በኡዋፔ በዩስ

. እጠፉለሁ ያለው ከታዘለበት ይጠፉል

.. ጥፉ ያለው ከመቀነት ወጥቶ ይጠፉል

950. በይረው ሰአይ ሎእን ካሎይ ዙሚናን ሄሚቴስ

. ታላቅየው ሲመቸው ታናሽየው ሳይድህ በእግሩ ይሄዳል

.. እቤት ዶሮ ሲታደረድ ከደጅ ቆቅ ይያዛል

951. በይራስ ምዮይ ባሽን ካሎይ አቻ ኪሲስ

. ታላቅየው የሚበላው የለው ታናሽየው ጥርስ ያበቅላል

.. የምበላው ሳጣ ልጄ ጥርስ አወጣ

952. በይርያ ዲሽን ካልያ ጌለውሱ

. ታላቅ እያለች ታናሽ ታገባለች

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

.. እድል ፈንታ ጥዋ ተርታ

.. እድል ነው ወይ በደል

.. የታደለ ተደላደለ

953. በይዙወው ኤፍዮጌ ሀ ዱንየን ቦይና ቶክያኮ አይበ ምከንዴ ጌስ

. ለመሸጥ የሚወስዱት እዚህ ጉብታ ላይ ጐደሬ ቢተክሉ እንዴት ይይዝ ነበር ይላል

.. ለራስ አያውቅ ነዳይ ቅቤ ለመነ ላዋይ

.. ልብ እንቅርት ይመኛል

954. በይዝያጌ ዋሀ ግን ሸምያጌ መረ ጌስ

. ሻጩ ዎሃ (በሬ) ሲል ገዥው ጥጃ ነው ይላል

.. ብልጥ ለብልጥ አይን ብልጥጥ

955. በደለን ሾጭዶ ከነይ ገክድ በደላ ሚነ ጌቴስ

. በበቆሎ የመቱት ውሻ ደርሶ በቆሎ አይበላም ይባላል

.. ዘንድሮ በቆሎ ሲበላ የተቀጣ ውሻ ሁለተኛ በቆሎ አይበላም

.. እባብ ያየ በልጥ በረየ

956. በደለይ አዬዳን ማሻ ግጤስ፣ አዋደን ቡቻ ኪሴስ

. በቆሎ እንደ እናቱ ምላጭ ይሰዳል፣ እንደ አባቱ ፂም ያወጣል

.. የዘሬን ብተው ያንዘርገረኝ።

957. በደለይ አተን ዶሌስ፣ ኤጩሬ አቻ ቦሮሼስ

. ቦቆሎ እዳሪ ላይ ይበቅላል፣ አይጥ ጥርሱን ይሸርፋል

.. እንዲያው በመላ ያህያ ፈስ ዳለቻ ነው

958. በደላ ምየ ከነ ዜርሺን ዎራቴስ

. በቆሎ የሚበላን ውሻ በቆሎው ሲዘራ ይገሏል

.. ከመቀደም መቅደም

959. በዴሰን መንደረይ ዜሬታፕ አቴስ፣

ጨጌነን መንደረይ ዩሎፕ አቴስ

. በአገመራ ጊዜ ሩቅ አገር የሄደ ከመገራት ይቀራል፤ በወር አበባ ጊዜ ሩቅ አገር የሄደ ከልጅ ይቀራል

.. ለሞፈር ቆራጭ እርፍ አይታየውም በግላጭ

960. ባለ ገለሰ ሾቤ ሾቤ ግዴነ ሀረ ገለሰ ተነ ኡታ ሾበርኪ ጌስ

. የበአል ቀን ግብጦ ግብጦ አይደለም ሌላ ቀን አምኾ በጋበዝ ከኝ ይላል

.. በችግር ቀን የተገኘ ቆሎ ከብርንዶ ይቆጠራል

961. ባሌ ጎዳ ባጭረይ ሚትን፣ ኢበደ ጎዳ ጲጲሌ ጩሌስ

. የባሌን ባላባት የቆጮ (የባጭራ) እንፍርፍር ይቸግረዋል፣ የኢባዳን ባላባት እንቁላል ያንቀዋል

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

962. ባረነው በይናረ መሻው ክየውሱ

. ምንም የሌላት የእርድ ቀን ታወጣለች

.. ምንም ቢመቱ አራድማ ሸምቱ

963. ባርዮበይ በይነ ኡረይ ገጮይ ጡቅን ጮመነው አሞቴስ

. የሚጐርሰው የሌለው ሰው ጉንጩ እስኪፈነዳ ለማኘክ ይመኛል

.. ትለብሰው የሌላት ትከናነበው አማራት

964. ባሮነይ በቅን፣ በበንቶነይ ቦክን፣ ዎልታምያ ጉዱንቶነይ ጌሌስ

. የባሮ ልጅ ሲሸሽ የድብ ልጅ በቆፈረበት የጉልበተኛው የአሳማ ልጅ ይገባበታል

.. አህያ የጫነውን ፈረስ ይበላል

965. ባሰ ጌልን በሪሮ ሀኖ ገውሱ

. ባሳን አግብቼ የፈለገ ነገር ይሁን ትላለች

.. ያበጠው ይፈንዳ

966. ባሳ አዝጌ ሲሬ ጢንቅየጋኔ ሰውየጋኔ ኤሬነ

. የባሳ አዝጌ (ስም) አፍንጫ የሚገማውንም ሆነ የሚሸተውን አያውቅም

.. ሰማህ አልሰማሁም አየህ አላየሁም

.. ግም ለግም አብሮ ያገግም

967. ባስ በይናጌ ግየይ ኤቆፓ ጌስ

. ለራሱ የሌለው የዛሬ ገበያ አይቁም ይላል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

968. ባስ ከልደይ ሽየ ቦል ኡትድ ሚጩስ

. የጠገበ አር ላይ ተቀምጦ ይስቃል

.. የጠገበ ሰው ራሱን አይጠብቅም

969. ባስ ግን ባጭ አሹዋ ቀንጤስ

. ለራስ ሲሉ ማጭድ ስጋ ይቆርጣል

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

970. ባስ ግን ባጭ ኡንጨ ቀንጤስ

. ለራስ ሲሉ ማጭድ ቆጮ ይቆርጣል

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

971. ባተይ በይነሰን ለክያ ታንክ ባተ ገውሱ

. ጋን በሌለበት እንስራ እኔ ጋን ነኝ ትላለች

.. ጋኖች አለቁና ምንቸቶች ጋን ሆኑ

.. ዋርካ በሌለበት እምቧጮ አድባር ይሆናል

972. ባታፕ ጢሪን ጣሮ ኩሚስ

. ከጋን ቢጠርጉ ገንቦ ይሞላል

.. ከድሃ ከመበደር ከባለፀጋ መለመን

.. ጋን ሲለቀለቅ ማድጋን ይሞላል

973. ባትያ በይነሰን ኩይጣርያ ተ አወ ገውሱ

. ጋን በሌለበት ምንቾት እኔ አባት ነኝ ትላለች

.. ጋኖች አለቁና ምንቾቶች ጋን ሆኑ

.. ዋርካ በሌለበት እምቧጮ አድባር ይሆናል

974. ባነ ሚሸይ ባታፔ ቤስ

. የሚሄድ ገንዘብ ከጋን ውስጥ ይሄዳል

.. ጥፋ ያለው አጥር ቀዶ ይጠፋል

975. ባነ እረይ ባና ቡኬስ

. የሚሄድ ዝናብ አቧራ ይዘንባል

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል

976. ባነ ደንገርሰይ ጠጴዋፔ ሚን ዴአነ ደንጋርሳይ ጤራፔ ሜስ

. የሚሄድ ዝሆን ስር ነቅሎ ሲበላ የሚኖር ዝሆን ቀንበጡን ይበላል

.. የሚያልፍ ውሃ አደረገኝ ድሃ

.. እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ትላለች እንሰሳ

977. ባነይ ብድንታ ሶጴ ጌስ

. አቧራ አመድን ትቢያ ብሎ ይሰድባል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል እንዲሉ

978. ባናረ ጋሼ ግን ዴአናረ አባ ገውሱ

. የምትሄድ ጋሼ ስትል የምትኖር አባባ ትላለች

.. የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት

.. አጉል ፍቅር ያመናቅር

979. ባወ ጋናፔ ጎይየ እሸይ ኬሀ

. የለም ከማለት ያበደ ወንድም ይሻላል

.. ሆድ ባዶ ይጠላል

.. ከሞተ አንበሳ ያለ እንስሳ

.. ወጥና ወንድም ማስፈራሪያ ነው

980. ባወ ጋናፔ ጎይየ እሸይ ደሮ

. የለም ከማለት ያበደ ወንድም ይሻላል

.. ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ

981. ባዮ ሚጣ ኤትያረ በ ነኤዮ ምዬ ሼምፐነሳ እምኬ ገውሱ

. ለራሷ አጥር ሰብራ የምታነድ ለልጇ ጐን መተኛ አልሰጥም ትላለች

.. ዝንጀሮ የራሷን ሳታይ በጓደኛዋ ትስቃለች

982. ባዮ ፐጤነይ በ ቦሎቴዮ ጠሌ ቦኬስ

. ለራሱ ያልዳነ ለአማቹ መድሃኒት ይቆርጣል

.. አንቃ ለራሷ አትበቃ ለሰው ጠበቃ

983. ባጋ መድገደ በሱዋ ቃቀተውሱ

. የራሷን በልታ ሽራፊ ትመኛለች (ትቀላውጣለች)

.. ትንሽ ሰው ትንሽ ነው

.. የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ

.. አልጠግብ ባይ ሲተፋ ያድራል

.. እንኳን የሸመተ ያረሰም አይችልሽ

984. ባጋስ ግን ባጭ ቀንጤስ፣ አሰባ ግን መሽ እጤስ

. ለራስ ሲሉ ማጭድ ይቆርጣል፣ ለሰው ሲሉ ቢላዋ እምቢ ይላል

.. ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ

.. ከራስ በላይ ንፋስ

985. ባጌ ባጋ በደ ኑጋ

. ምንም ቢሆን ዘመድ ከዘመዱ፣ ምንም ቢሆን የእልህ መወጣጫ

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

986. ባጌ ዮት ኤከነው ዴኦ

. የራስ ዘመድ ይኑር ለመመካከር (ለመነጋገር)

. ምንም ቢሆን የኔ የሚሉት ይሻላል

.. አኝከህ አኝከህ ወደዘመድህ ዋጥ

.. ምንም ቢከፋ ዘመድ ምንም ቢጠብ መንገድ

987. ባጭራ በሼ ሜኤስ ከፉ ግሚረ ኦጌ ዱጤስ

. የእንኩሮ ምጣድ ይሰበራል፣ የከፋ ጊሚራ መንገድ ይቋረጣል

.. ያበጠው ይፈንዳ

.. ለሁሉም ጊዜ አለው

988. ቡለቸን አቀደ ይየ ምሽርያ ተናቶ እንቴነ ዋን ነምስ ነምሲ ገውሱ

. ሰርግ ቤት አድራ የምትመጣ ሴት ልጆቹ እንዴት ይርባችኋል ትላለች

.. ያልተነካ ግልግል ያውቃል

989. ቡሉዋ ተልአነ ብያረ ቡሎ ምንጂናሮ ዎነ አ አይ መጫሴ ገውሱ

. ብቅል ለመበደር የምትሄድ ብቅል ያላስቀመጠችውን ምን ሴት ትባላለች ትላለች

.. ሰነፍ ሴት እድል የላትም ለንብረት

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ

990. ቡልኡሽ ኡንጨይ ባወሽን ኡንጫ ሼንዴራ መውሱ

. ቢልኢሼ ቆጮ ሳይኖራት የቆጮ ገንፎ ትበላለች

.. ይታደሏል እንጂ አይታገሉም

991. ቡር ባረነ ግን ቦረ አሾይ ግዴነ፣ ማር ግረነ ግን መረ አሾይ ግዴስ

. ጠርጌ ልጉረስ ካሉ የበሬ ስጋ አይበቃም፣ በማዕረጉ ሲያድሉ የጥጃ ስጋ ይበቃል

.. መተዛዘን ካለ አንድ እንጀራ ለአስር ይበቃል

992. ቡቀይ ጫላ ከሬስ

. የበሰበሰ ኮምጣጣን ይንቃል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

993. ቡቁሬ አው በይ ግን ሳርደ ሰአን ዎትዶጋ ቦለን ዎተነው በለንጎ አምቦምሶ በይስ ገውሱ

. ቡቁሬ (ስም) የት ትሄጂያለሽ? ቢሏት ሳርዴ መሬት ላይ ያስቀመጠችውን ለመስቀል አምቦሜ ባላንጐ ቤት እሄዳለሁ ትላለች።

.. ከሞኝ ሸክም ሞፈር ቀንበር ይቆረጣል

994. ቡቻ ትስትን ትረን ጦኪስ

. አገጭ ላይ የተቀቡት ደረት ላይ ይንጠባጠባል

.. ለሃጥአን የመጣ ለዓድቃን ይተርፋል

.. አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ

995. ቡቻመይ ጮይሽን ቢሶፖ

. ባለጺም (ጺማም) ሲያስታውከው (ሲያስመልሰው) አያድርስ

.. እንኳን ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ

996. ቡንያ ኡሉወን ጢሌ ዴኤስሽን ተ ኡሉወን አይብከ ባወ ጌስ

. በበጠጥ ሆድ ውስጥ ዱቄት ሲኖር እኔ ሆድ ውስጥ ምንም የለም ይላል

.. ሞኝ አይታወቅብኝም ባይ

.. አፍ ሲያብል ልብ ይታዘባል

997. ቡካ በው ዞልያ መውሽን በ ነአ ነአ ድቸን ኤሀውሱ

. ቡካ ለራሷ የምትበላው አንድ ዝግን ሲሆን የልጇን ልጅ ለማሳደግ ታመጣለች

.. አባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል

.. ወግ ነው ሲዳሩ ማልቀስ

998. ቡከይደ ሱይቅያረ ጋጨይደ ዋነንዴ?

. ስትወቃ የዘፈነች (የምታኗል)፣ ኋላ ስትፈጭ ምን ትሆን ይሁን?

.. ለትዝብት ያብቃን

999. ቡከይዳ ቡላለይ፣ አገይደ ሳሜተይ፣ ከተይደ ኮሸተይ

. እየናጥሽ አመዳም እየጠመቅሽ የምትጠሚ እያበሰልሽ የምትራቢ

.. ስስታም አንድ ያንቀው፣ አንድ ይወድቀው

1000. ቡከያ እራኔ ዩልየ መችዮኔ እጠፐ

. ዝናብንና የምትወልድ ሚስት አትጥላ

.. ቢያስቀዝንም ጮማ ይሻላል

1001. ብለሄ በርካ ባናረ ገለስ ተነ የሼስ ገውሱ

. በሌሊት ብቻዋን የምትሄድ ቀን እፈራለሁ ትላለች

.. ሞኝ አያውቁብኝ ባይ

.. ላያውቁሽ ታጠኝ

1002. ብረስሰነው ኤፍን ጠመነው አዴስ

. ለማስጠቃት ቢወስዱት ሊጠባ አለፈ

.. ያመኑት ፈረስ በደንደስ

1003. ብረተይኔ ዎንጠፈይኔ ሜለ አይስ ኤሬነ

. ጠመንጣና ብልት ጦም አያሳድሩም

.. ያለው ይበላል የሌለው ይፈዛል

1004. ብርሸ መግን ሉክ ሚስ

. ፈተህ ብላ ቢሉት በስቶ ይበላል

.. የለመደ ልማድ ያሰርቃል ከማዕድ

1005. ብሮን ብትያረ ብረሳ ዎረውሱ፣ ብሮን ዶምየ ካዮይ ጌላእዮ አሞቴስ

. ጀማሪ ሚርተኛ እርጉዝ ላም ትገድላለች፣ ጀማሪ ጠንቋይ ልጃገረድ ያልማል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጢጥ

.. ያላወቁ አለቁ

1006. ብሮን ዶምየ ካዮይ ጌለእዮ አሞቴስ

. ገና የሚጀምር ጠንቋይ ልጃገረድን ያልማል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጢጥ

1007. ብተ ብሉ ከሬ ጎሮሞትያ አንቴ አጼስ

. የሚርተኛው (ደንቃራ) ቢሉ ደጅ ቡዳው አንቴ ደፍሮ ይሄዳል

.. አህያ ላህያ ቢራገጡ ጥርስ አይሳበሩም

1008. ብተንቸይ ሄከ ጡመን ዱሬስ

. ሚርተኛ በድንግዝግዝ ጨለማ ይጨፍራል

.. ሞኝ አይታወቅብኝ ባይ

1009. ብተንየው ተ ኔነ ጨይሽን ኔነ አይቤ ሚችየይ

. ሰውየው እኔ አንተን እየሰደብኩህ አንተን ምን ያስቅሃል

.. እካስ ያለ ታግሶ እፀድቅ ያለ መንኩሶ

.. መተው ነገሬን ከተተው

1010. ብተንየው ፕለይ ባወሽን ሞይትልየው ኮርማ ሹከ ጌስ

. ለመድሃኒት አይብ የሌለውን ለውቃቢህ ወይፈን እረድ ይለዋል

.. በቅሎ ግዙ ግዙ አሞሌ ላያግዙ

.. በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት

1011. ብተይ ብሊሴቴስ፣ ዱርሰይ ድናቁቴስ

. ሚርተኛው ይተራመሳል ዳንሱን ያቀልጣል

.. ክፉ አድራጊ ተኝቶ አያድርም

1012. ብድንተይ ባና ሶጼ ግ ቦሬስ

. አመድ ዱቄትን ትቢያ ብሎ ይሰድባል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. መታፈር በከንፈር

1013. ብድንተይ ቦቅንታ ታውሌ ጌስ

. አመድ ኖራን አብዱ ይላል

.. ዘመድ ከዘመዱ አህያ ካመዱ

.. ለራስ ሲቆርሱ አያላንሱ

1014. ብድንተይ ጢልያ ቦቅንተይ ጌስ

. አመድ ዱቄትን ነጫጭባ ይላል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

1015. ብድንተይ ጢልያ ከሬስ

. አመድ ዱቄትን ይንቃል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

1016. ብድንታ ምያረ ጢልያ ምያሮ ቦረውሱ

. አመድ የምትበላ ዱቄት የምትበላውን ትሳደባለች

.. አመድ በዱቄት ይስቃል።

1017. ብድንታ ጢሌ ሙሌ ገለስ ከሬስ

. አመድን ዱቄት ሁል ጊዜ ይንቀዋል

.. አመድ በዱቄት ይስቃል

.. ይሉሽን በሰማሽ ገበያም ባልወጣሽ

1018. ቢርቢርያ ኩትያ ብኪ ኤከውሱ

. የተንቀዠቀዠች ዶሮ ዱላ ትቀምሳለች

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ጠንቁላ ትመጣለች

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

1019. ቢቅቢቅያ ከንያ ብኪ ኤከውሱ

. የተቅበጠበጠች ውሻ ብትር ትቀምሳለች

.. አለማረፍ ጣር ያበዛል

.. አላርፍ ያለች ጣት አር ትጠነቁላለች

1020. ቢብሶይ ጠሌ ኡይን አጋቶይ ጉሰነው ዎጤስ

. ቢቢሶ ኮሶ ጠጥቶ አጋቶ ለቅዘን ይሮጣል

.. አባ ኩሶ ጠጥተው አቃቢታን አሻራት

.. አንዱ ሊበላ ሌላው ያጎበጉባል

1021. ቢተው ዴእየ ደንደያ ደንደይድ ፔኤስ

. እንደመሬት ታማሶ ይውላል

.. ሆድ ይሰፋል ከሁዳድ

1022. ቢተይ ማሌነሽን ጥተ ቀቼስ

. አፈሩ ሳይስተካከል ጥቀርሻ ያስራል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቂጢጥ

.. ሳይገድሉ ጎፈሬ ሳያረጋግጡ ወሬ

1023. ቢተይ ባተው ፕርዴስ

. አፈር ለጋን ይፈርዳል

.. የአይጥ ምስክር ድምቢጥ

1024. ቢተይ ብትዮይ አፑኔ

. ስንቱን ነው አፈር የበላው

.. ስንቱ እንደዋዛ ቀረ

.. የሞት በደለኛ አይያዝ በዳኛ

1025. ቢተይ ትርያ ጮዬስ

. አፈር ደም (ጉበት) ያስታውካል

.. ልብ ያሰበውን አፍ ይናገራል፣ አይን ያየውን እጅ ይሰራዋል

1026. ቢተይ ጩግድ ቁጠርሳ ዬሌስ

. አፈር (መሬት) ሲያረጅ ጃርት ይወልዳል

.. መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል

1027. ቢተይ ጩግድ ኦጩዋ ዬሌስ

. መሬት ሲያረጅ ፍልፈል ይወልዳል

.. መሬት ሲያረጅ መጭ ያበቅላል

1028. ቢታ ሜጭን ቢተይ ጐጌስ

. አፈር ቢያጥቡት አፈር ይፈሳል

.. ታጥቦ ጭቃ

.. ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ

1029. ቢታ ሱራ ቢታ ቦረይ ኪሴስ

. የአገርን ሰርዶ የአገር በሬ ያወጣል

.. ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ

1030. ቢታ ኦቴነን ጎተራ ኤሰነ ጌስ

. መሬት ሳያርስ ጐተራ አቆማለሁ ይላል

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

.. ለአፍ ዳገት የለውም

1031. ቢቲ ባወሽን ተላለ በንበሬ ጋጨውሱ

. ተለሌ ምንም ሳይኖራት በርበሬ ትፈጫለች

.. ወጡ ሳይወጠወጥ ወስከምቢያው ቁጢጥ

.. የምትለብሰው የሌላት የምትከናነበው አማራት

1032. ቢታን ሳሆይ ሃኮ ሃርጌን ጉሶይ ሃኮ

. በሽታ ከአገር ይጥፋ፣ ከበሽታም ተቅማጥ ይጥፋ

.. ከበሽታም በሽታ ይመረጣል

1033. ቢኬ ግዮ አግያ ቶሆይ ኤፈስ፣ ሚኬ ጊያ ከታ ናሚሲ ሚዜስ

. አልሄድም ያሉት ቦታ እግር ይወስዳል፣ አልበላም ያሉትን እህል ረሃብ ያስበላል

.. የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል

.. ለሁሉም ጊዜ አለው

1034. ቢደ መችያ በይዳ ከና ኤሀውሱ

. የሄደች ሚስት የጠፋ ውሻ ታመጣለች

.. የገበያ ግርግር ለሌባ ይመቻል

.. ዳን ላለው መድሃኒት አለው

.. ግርግርታ ለሌባ ደስታ

1035. ቢድ ይያጌ ዎዘነ፣ ቦሰን አትያጌ ቦአ

. ሄዶ የሚመለስ ልብ ነው፤ በሄደበት የሚቀር መላጣነት ነው

. ገንዘብ የሚገኘው በሰላላ፣ ልብ የሚገኘው በስልላ

1036. ቤትድ ዬስ ዎዘነይ

. ልብ ኰብልሎ ይመለሳል

.. ብልህ ሰው ከስህተቱ ይማራል

.. የማይሳሳት የማይሰራ ሰው ነው

1037. ቤቴ ሀች ዩድ ዎንተን ታው አያነይ ኔነ ሱጐ ጌስ

. ስደተኛ ዛሬ መጥቶ በማግስቱ ያባቴ ውታቤ ይግፋህ ይላል

.. ከኋላ የመጣ ዓይን አወጣ

1038. ቤቴስ ቤሌ ባ

. ስደተኛ ኩርፊያ የለውም

.. ልጅና ለማኝ የሰጡትን ይቀበላል

.. ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ ቢጭኑት አህያ ቢቀመጡት ፈረስ

1039. ቤን ምሽርያ ከዎ ጌለነ ገይዳ ጌሎፔ አተውሱ

. ድሮ ሴትየዋ ንጉስ አገባለሁ ስትል ጭራሽ ሳታገባ ትቀራለች

.. ምኞትና ጉም አይጨበጥም

1040. ቤን አይጋኮ መለን ሀርያ ሱቆይ ቡለ ጌስ

. ድሮ በመላ ያህያ ፈስ ቡላ ነው ይላል

.. እንዲያው በመላ ያህያ ፈስ ዳለቻ ነው ይባላል

1041. ቤን ከውዋ አይፍያ ዎጭሽን ተ ስጵንታ ሞሮፐ ጌስ

. ድሮ የንጉሱን ዓይን ሲቦጠቡጥ ቅንድቤ እንዳይበላሽ ይላል

.. ነጋዴው ውሃ ሲወስደው ሚስቴን አደራ ይላል

1042. ቤአይ ኤሬስ፣ ጩገይ ኤሬነ

. ያየ ያውቃል፣ የሸመገለ አያውቅም

.. ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል

1043. ቤእደይ ኤሬስ፣ ሚእደይ ዶጌስ

. ያየ ያውቃል የተሰበረ ያነክሳል

.. ያየ ይናገራል የተወለደ ይወርሳል

1044. ቤጤ ምታ ቆኢድ ፔእን ቀረቶ ጊድ ጎደን ከቁቴስ

. ጠገራ እንጨት ሲፈልጥ ውሎ ስለታም እንዲሆን ግድግዳ ላይ ይሰቀላል

.. ሞኝ ቢሸከም የበላ ይመስለዋል

1045. ቦለን ደደይ የይዮ ምታ ዝንእን ሰኣን ከነይ ጣሌስ

. በቁሙ መብረቅ የሚፈራውን እንጨት ሲተኛ መሬት ላይ ውሻ ይራመድበታል

.. አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል

.. የወደቀ እንጨት ምሳር ይበዛበታል

1046. ቦለን ጎንግያ ጎዳ ናእያ ዎለይተን ተምቡዋ ጎዳ ነኣ ጌለውሱ

. ቦላ የመክተፊያ ጌታ ልጅ ወላይታ የትምባሆ ባለቤትን ልጅ ታገባለች

.. ቢጤው ከቢጤው

.. ቂጢኛም ከውርዴ ይዞራል

1047. ቦለይ ኪህን ቦርቱወን ዲቼቴስ

. ሰውነት ሲደላ በኮርች ይታከኳል

.. ካልጠገቡ አይዘሉም ካልዘለሉ አይሰበሩም

.. ከወፈሩ ሰው አይፈሩ

1048. ቦላ ጉሌትድ ገርሳ ከሎቴስ

. ላዩን ተከናንቦ ታቹን ይራቆታል

.. ሞኝ አይታወቅብኝ ባይ

.. የምታጠልቀው የላት የምትከናነበው አማራት

1049. ቦላረ ቦጥድ ገርሳረ መሱንጤስ

. ከላይ ነጭ ከውስጥ ቁስል

.. ውስጡን ለቁስ

1050. ቦላረ ጉሌተውሱ ገርሳረ ከሎተውሱ

. ከላይ ትከናነባለች ከታች ትራቆታለች

.. የምትለብሰው የላት የምትከናነበው አማራት

.. ቢከፍቱት ተልባ

1051. ቦሉዋ ዱለው ቦራ ሹክ ሚስ

. ለአማች ይሉኝታ ሲል በሬውን አርዶ ይበላል

.. ይሉኝታ የራስ ዐሊን ቤት የፈታ

1052. ቦሉዋ ዱለው ቦራ ዱሴስ

. ለአማች ይሉኝታ ሲል በሬ ያልባል

.. ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ

1053. ቦልአይ ቦር ዱሴስ

. ችኩል በሬ ያልባል

.. የቸኮለች አፍሳ ለቀመች

1054. ቦሊምያ ቦሎትዮ ቀጠረውሱ

. የምትቀብጥ ምራት አማቷን ትገርዛለች

.. ልጅ ለናቷ ምጥ አስተማረች

1055. ቦሌ በር ምሹወው በሽያ ሰጤስ

. አንበጣ ሲጠበስ ምጣድ ይነክሳል

.. እልኸ ምላጭ ያስውጣል

. እልኸኛ መዥገር ቁርበት ላይ ይጣበቃል

1056. ቦሎ የሻስ ሹጎ ጮሚቴስ

. ለአማች ተፈርቶ ለስላሳ (ሙቅ) ያኝኳል

.. አማችና ጋሻ ካልሰገዱለት አይወድም

1057. ቦሎረ ቦንኮሌትሽን ሚገ፤ ጠንታረ ፒኤስ

. በአማች መስተንግዶ ሰበብ ላም ሳትታለብ ትውላለች

.. ላይጠቅመኝ ቂጤን አረጠበኝ

.. ላይጠቅም ጋሻ ቂጥ ያስወጋል

1058. ቦሎሶ ቦለን ቦሮቆ ሀሬ አ ጌዱዋ ካልያይ ሽፋረ ጎሴ

. ቦሎሶ ላይ ቦቃ አህያ እሱን የተከተለ የመሸመቻ ቅል

.. አባም ሰው ሆኑና ሰው ገደላቸው

1059. ቦሎሶን መጫረ ቶግዮ ማጣነይ ተነ ጪራቅያ አልኢ?!

አዩ አነ ጌስ

. እቦሎሶ ሴቷ የምትቀመጥበት አጋሰስ ለኔ ለጨራቂው (ቦታ) ይወደዳል! ወይኔ ይላል

.. ቀን ከጣለው ሁሉ ይጥለው

1060. ቦሎሶን ቦከነ ብየ ከይሶይ ቦድቲን ሰሮ ጌስ

. ቦሎሶ ሊቆፍር የሚሄድ ሌባ ቦዲቲ ላይ ..ንደምናችሁ ይላል

.. ማነህ ባለ ሳምንት ያስጠምድህ ባስራ ስምንት

1061. ቦሎሶን ዶርሳ ያንቻ – የቦሎሶን የበግ ድብዳብና

ኮይሸን ጠዲያ ሎሃ – የኮይሻን የጐማ ለኮ

ገትየይ ፐራ ዘኩዋ – የሚያገናኘው የ ረስ ጀርባ

.. ፃድቃን ሳይቀጣጠሩ ይገናኛሉ

.. የሺ ፍልጥ ማሰሪያው ልጥ

1062. ቦሎትዮ ቦንቻረ ለሶሮ፣ ቦንቸደ ቀስ ፖ ሌነይ ሙታሮ

. አማችን የምታከብር ላሰሮ (ጨዋ)፣ አክብረህ ደግሞ የማትዘልቅ ሙታሮ (ባለጌ)

.. የማያዛልቅ ጸሎት ለቅስፈት

1063. ቦሎትዮ ነአ መቸያ ጢነውሱ

. አማትየዋን የልጅ ሚስት ታወግዛለች

.. አማትና ምራት ሳይስማሙ መሬት

.. ከኋላ የመጣ ዓይን (ቀንድ) አወጣ

1064. ቦሎቴንተ ሀይቆይ ቱመ ግዲን አፈለይ ታጋ ግድኤሬኔ

. የአማቴ ሞት እውነት በሆነና ልብሱ (ከፈኑ) የኔ ቆዳ በሆነ

.. አማትና ምራት እሳትና እራት ሳይስማሙ መሬት

.. የነብር ዓይን ከፍየል የፍየል ዓይን ከቅጠል

.. የጠሉት ሰው አር ከሆዱ ውስጥ ይገማል

1065. ቦሎይ ቆጥን ቦሎትያ ዬለተውሱ

. አማች ሲፈሳ አማት ታፍራለች

.. ሞኝ ባያፍር የሞኝ ዘመድ ያፍር

1066. ቦሎይኔ ቦርኮተይኔ ዎንተን አቲችድ ቤቴነ ገውሱ

. አማችና ትራስ በጧት ካመለጠ አይገኝም ትላለች

.. ልጅና መንገድ የጥዋት ነው

1067. ቦረይ ቦላነ ከዶይ ካላነ ግዱወን ዎተ አተ

. በሬው ቦላ (ቦታ) ሞፈር ካለ (ቦታ) እመሃል ሂድ አሳልፍ (ውጣ ውረድ)

.. ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አላይ

1068. ቦረይ ቦራራ ዞሬትድ ቀምባራ ሚንቲስ

. በሬ ከበሬ ጋር ተማክሮ ቀንበር ይሰብራል

.. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር